# ትምህርት ቤቶችን ማዕከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ

ትምህርት ሚኒስቴር

ሰኔ 2008 ዓ.ም

| ተራ ቁጥር | ማውጫ---------------------------------------------------- | ገፅ |
|---|---|---|


| | | |
|---|---|---|
| | መግቢያ----------------------------------------------------------------------- | 4 |
| | **ክፍል አንድ** | |
| 1.1. | የገጠር ትራንስፎርሜሽን ያለበት የሁኔታ ትንተና---------------------- | 5 |
| 1.1.1. | የማኅበራዊ ጉዳዮች ሁኔታ--------------------------------------------------- | 5 |
| 1.1.2. | የኢኮኖሚያዊ ሁኔታ--------------------------------------------------------- | 7 |
| 1.1.3 | የፖለቲካዊ ሁኔታ------------------------------------------------------------ | 8 |
| 1.2. | ከሁኔታ ትንተና የተወሰዱ መደምደሚያዎችና ዋና ዋና ጉዳዮች----- | 9 |
| 1.3. | የፓኬጁ አስፈላጊነት-------------------------------------------------------- | 10 |
| | **ክፍል ሁለት** | |
| 2.1. | የፓኬጁ ዓላማ--------------------------------------------------------------- | 11 |
| 2.1..1. | አጠቃላይ ዓላማ-------------------------------------------------------------- | 11 |
| 2.1.2. | ዝርዝር ዓላማ---------------------------------------------------------------- | 11 |
| 2.2. | ትምህርት ቤቶችን ማእከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን በጎልማሶች ትምህርትና ስልጠና ዋና ዋና የትኩረት መስኮች-------- | 12 |
| 2.2.1. | የንባብና የጽህፈት ክህሎትና የሙያ ስልጠናዎች----------------------- | 12 |
| 2.2.2 | የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና መልካም አፈስተዳደር-------------- | 12 |
| 2.2.3. | የጤና አጠባበቅ-------------------------------------------------------------- | 12 |
| 2.2.4. | እርሻና ተፈጥሮ ሀብት------------------------------------------------------ | 12 |
| 2.2.5. | የእንሰሳት እርባታ----------------------------------------------------------- | 12 |
| 2.2.6. | የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ----------------------------------------------- | 12 |
| 2.2.7. | ቱሪዝም፣ ባህልና ቅርስ----------------------------------------------------- | 12 |
| 2.2.8. | ሥርዓተ ጾታ----------------------------------------------------------------- | 13 |
| 2.2.9. | ስፖርት፣ ባህላዊ ጫዋታዎችና መዝናኛዎች---------------------------- | 13 |
| 2.2.10. | ማኅበራዊ ደህንነት-------------------------------------------------------- | 13 |
| 2.2.11. | ከተማ ልማትና ቤቶች-------------------------------------------------------- - | 13 |

**ክፍል ሦሥት**

3.1 ትምህርት ቤቶችን ማእከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን በጎልማሶች ትምህርትና ስልጠና የትኩረት መስኮች፣ ዝርዝር ይዘቶች፣ የማስፈጸሚያ ሥልቶች፣ ፈጻሚ አካላት፣ የሚፈጸምበት ጊዜና የበጀት ምንጭ------------------------------------------------------ 14

3.2. የውጤት አመላካቾች /የሚጠበቁ ውጤቶች/------------------------------ 21

**ክፍል አራት**

4.1. የፓኬጁ ማስተግበሪያ ስልቶች-------------------------------------------- 22

4.2. የፓኬጁ ተጠቃሚዎች------------------------------------------------------ 23

4.3. ትምህርት ቤቶች ለዚህ ተግባር ለምን ተመረጡ?----------------------- 23

4.3.1. የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ ለመተግበር በትምህርት ቤቶች የሚኖረው አመራርና አደረጃጀት------------------------------------------- 24

4.3.2. በትምህርት ቤቶች የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ ለመተግበር የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነት------------------------------------------ 25

4.4. ትምህርት ቤቶችን ማዕከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ክትትልና ድጋፍ------------------------------------------------------------ 26

4.4.1 የክትትልና ድጋፍ ዓላማ--------------------------------------------------- 36

4.4.2.. የክትትልና ድጋፍ አግባብ------------------------------------------------ 27

4.5. የግንኙነት መረብ መዘርጋትና አጋርነትን ማጠናከር--------------- 27

## መግቢያ

የሀገራችን 84 በመቶ የሚሆነው የገጠሩ ህዝብ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርና ላይ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ይህን በግብርና ላይ ጥገኛ የሆነውን ኢኮኖሚ ለመለወጥ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም ሀገራችን ላለፉት 25 አመታት በዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እንዲሁም በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግባለች፡፡ለአብነት ያክል ላለፉት አስር ተከታታይ አመታት በአገራችን ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት መመዝገቡ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፉ ያስመዘገበችውን እድገት አጠናክሮ በመቀጠል በ2017 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የተለያዩ ጥረቶች በመደረግ ላይ ነው፡፡

ኢኮኖሚያችን በከፍተኛ የእድገት ግስጋሴ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በተለይ በገጠሩ አካባቢ አሁንም ሰፊ የሆኑ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት እንዲቻል በገጠር የሚገኙ ት/ቤቶችን በዋነኛነት በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ለህብረተሰብ የአገልግሎ መስጫ ማእከላት በማድረግ ለገጠሩ ማህበረሰብ የትራንስፎርሜሽን ሂደት አጋዥ እንዲሆኑ ማድረግ ቁልፍና ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ እየተመዘገበ ያለው ፈጣን ዕድገት ድህነትንና ሥራ አጥነትን በመቀነስ ረገድ ውጤታማ ቢሆንም ከድህነት ያልተላቀቁ የሀገራችን ህዝብ ቁጥር አሁንም ከፍተኛ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚያስፈልግ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የገጠሩን ኅብረተሰብ የኑሮ ዘይቤ በመቀየር ትራንስፎርም ለማድረግ ትምህርት ቤቶችን ማዕከለ በማድረግ የሚተገበር ይህ ፓኬጅ ተዘጋጅቷል።

ፓኬጁ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በክፍል አንድ የገጠሩ ትራንስፎርሜሽን ነባራዊ የሁኔታ ትንተና ቀረቧል፡፡ በክፍል ሁለት የፓኬጁ አላማና የትኩረት መስኮች የተዘረዘሩ ሲሆን በክፍል ሶስት የፓኬጁ ዝርዝር ይዘቶች፣ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ስልቶች እንዲሁም ፈጻሚ አካላትና የሚፈጸምበት ጊዜ ተዘርዝሮአል፡፡በመጨረሻም በክፍል አራት ዋና ዋና የፓኬጁ የማስተግበሪያ ስልቶችና በትምህርት ቤቶች የሚኖሩ አደረጃጀቶች ተካትቶ ቀርቧል።

ይህ ፓኬጅ የተዘጋጀው በት/ሚኒስቴር አስተባባሪነት ሲሆን በሂደቱም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከአስር ባለይ የሚሆኑ ፌደራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች የሶስት ክልል ት/ቢሮዎች እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአጠቃላይ 25 የሚሆኑ ባለሙያዎችና ሀላፊዎች ተሳትፈዋል፡፡ለዝግጅት ሂደቱ ግብአት እንዲሆን ተሳታፊዎች ከመ/ቤታቸው ሃላፊነት አንፃር በፓኬጁ ሊካተቱ ይገባቸዋል ያሉአቸውን ርእሰ ጉዳች በመለየት እንዲሁም ሰነዶች ይዘው እንዲመጡ የተደረገ ሲሆን ይንንም መሰረት በማደረግ ሰነዱ በጋራ ሊዘጋጅ ችሎአል፡፡በተጨማሪም ከሁሉም ክልል ትምህርት ቢሮዎች ባለሙያዎች በተገኙበት የተዘጋጀውን ሰነድ እንደገና እንዲተችና እንዲዳብር የተደረገ ሲሆን ረቂቅ ሰነዱን ለከፍተኛ አመራሩ በማቅረብ በተሰጠው

ግብአት መሰረት በማስተካከል አሁን ያለበት ደረጃ ማደረስ ተችሎአል፡፡/የተሳታፊ አካላት ዝርዝር በተቀፅላ አንድ ተመልክቶአል/

# ክፍል አንድ

## 1.1. የገጠር ትራንስፎርሜሽን ያለበት የሁኔታ ትንተና

### 1.1.1. የማኅበራዊ ጉዳዮች ሁኔታ

በአገራችን ለተያዘው የልማት እንቅስቃሴ ትምህርት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ሰፊ በዕውቀት የዳበረና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል በመገንባት የሀገራችንን ኢኮኖሚ፣ የህበረተሰቡን የኑሮ ደረጃና የፖለቲካ ተሳትፎ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመሠጠቱ ባለፉት አስርት አመታት በርካታ ትምህርት ቤቶችን በገጠሩና በከተማ እድሉ ባልደረሰባቸው አካባቢዎች በመገንባት እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ በርካታ ህጻናት የትምህርት እድል እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በ1983 ዓ/ም ሶስት ብቻ የነበሩት የዩኒቨርስቲዎች ቁጥር በአሁኑ ሰአት ወደ ሰላሳ ሶስት የደረሱ ሲሆን በአጣቃላይ በትምህርቱ ሴክተር ከሃያ ሰባት ሚሊዮን በላይ ዜጎቻችን ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ እድሜያቸው ከ15-60 ዓመት የሆኑ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የትምህርት እድል ያላገኙ ወጣቶችና ጎልማሶች መኖራቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ለነዚህ የትምህርት እድል ላላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ትምህርትን ማዳረስ ብሎም የትምህርትን ጥራትና ፍትሐዊነትን ማስጠበቅ ወሣኝና አማራጭ የሌለው እርምጃ በመሆኑ በሁሉም ዘርፍ እስከ ታችኛው እርከን ድረስ የሰው ሃይል ለማልማት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተዘርግቶ ሲተገበር ቆይቷል። በዚህም መሰረት ከሰባት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ጐልማሶችን ከማይምነት ነፃ ማድረግ የተቻለና ከዓመት ዓመት አፈጻጸሙ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡትን ግቦች ማሳካት አልተቻለም፡፡

በዚህም በኘሮግራሙ ትግበራ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የጐልማሶች ትምህርትን የሌሎች ልማት ሥራዎች ማጣለጫና ወሣኝ ጉዳይ መሆኑን ጠንቅቆ አለመረዳት፣ ክልሎች ተገቢውን አደረጃጀትና የሰው ሃይል መድቦ አለመንቀሳቀስ፣ በቂ በጀት አለመመደብ፣ በየደረጃው ያሉ የተለያዩ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ቅንጅታዊ አሠራር የላላ መሆን፣ ለፕሮግራሙ ትግበራ ሚና አላቸው ተብለው በየደረጃው የተለዩ የሕዝብ ክንፎች

ትርጉም ባለው መልኩ አለመግተፍ፣ በአመራሩና በፈፃሚው የሚታዩ የአመለካከትና የቁርጠኝነት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት በጤና ዘርፍ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ዜጋ ለማዳረስ እንዲቻል በስታንዳርዱ መሠረት ጤና ኬላዎችና ጤና ጣቢያዎች በሁሉም አካባቢዎች ተገንብተዋል፡፡ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት የሚሰጡ 40 ሺህ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ተሠማርተዋል፡፡ መካከለኛና ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎችም በስፋት በማሠልጠን ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል፡፡

የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ማስፋፋት፣ የቅድመና የድህረ ወሊድ ጤና አገልግሎት ሽፋን ማሳደግ፣ በባለሙያ የተደገፈ የወሊድ አገልግሎት ማሳደግ እና የእናቶችና ህፃናት ጤና በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ተችሏል፡፡የሕፃናት ሞት በሁለት ሦስተኛ መቀነስ የሚለውን የምዕተ ዓመቱን ግብ ሀገራችን ከጊዜው ቀድማ ማሳካቷ ተረጋግጧል፡፡የእናቶች ሞትን በሦስት አራተኛ መቀነስ በተመለከተም በመንግስት በተከናወኑ ሥራዎችና በዋናነት በሴቶች የተደራጀና የተቀናጀ ንቅናቄ ሀገራችን የምዕተ-ዓመቱን ግብ ለማሳካት ከተቃረቡት በጣም ጥቂት አገራት መካከል ተሰልፋለች፡፡ በጤና ዘርፍ ቀጣይ ትኩረት ከሚያሹ ጉዳዮች መካከል የህፃናትና የእናቶች ሞት አሁንም ከፍተኛ በመሆኑ የተጀመረውን ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል፣ አንዱና ዋና ነው፡፡

ለወጣቶች የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ 4.89 ሚሊዮን ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች ተደራጅተው በተለያዩ የስራ መስኮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡በግብርና የሥራ መስኮች 2.21 ሚሊዮን እንዲሁም ከግብርና ውጭ በሆኑ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች 2.43 ሚሊዮን በመሰማራት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ለወጣቶች የተለያዩ የስራ እድሎችን በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ቢሆንም አሁንም ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የገጠር ወጣቶች የስራ እድል ማግኘት አልቻሉም፡፡

በዕቅዱ ዘመኑ በ553 ወረዳዎች 1684 የወጣት ማዕከላት በማስፋፋት በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ነባሮችን ጨምሮ የማዕከላት ቁጥር 2284 ደርሷል፡፡ በነዚህ ማዕከላት 6.74 ሚሊዮን ወጣቶች የተለያዩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ሆኖም

ግን በገጠሩ የሀገራችን ክፍል የነዚህ ማእከላት እኩል ተደራሽ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡

በሀገራችን የተፈጠረው ፈጣን ልማት ዜጎች በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሰማሩ፣ ልማታዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉና በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ከዚህ እድገት ጋር በተያያዘ የማህበራዊ ደህንነት የማረጋገጥ ስራዎች ከገጠሩ ማኅበረሰብ ፍላጎቶች ጋር አቀናጅቶ ማከናወን ይገባል። በተመሳሳይ ሁኔታም ከአደጋ እና ከጤና ጠንቅ/ጉዳት የተጠበቀ ምቹ የስራ አካባቢን መፍጠር ለስራ ውጤታማነትና ምርታማነት እንዲያድግ ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው።

ባለንበት ወቅት የገጠር ክፍል ጎልማሶች እየተሳተፉባቸው የሚገኙ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የስፖርት ውድድሮች በስፋት እየተካሄዱ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡ይህም የጎልማሳውን ጤንነት በማሻሻል፡ እንዲሁም ማህበራዊ መስተጋብር ጤናማ ከማድረጉም በተጨማሪ በምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ የሚኖረው ፋይዳ የጎላ ነው፡፡ጎልማሶች በህይወት ዘመናቸው ያካበቷቸውን የተለያዩ ተሞክሮዎች፣ የጋራ ባህልና ወግ ልማዳቸውን ለሌሎች ለማካፈል እንዲሁም የአካል ብቃታቸውን ለማሳደግ በተለያዩ የመዝናኛና ስፖርታዊ የውድድር መስኮች ሊሳተፉበት የሚያስችል ሁኔታ በስፋት ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡

### 1.1.2. የኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

የገጠሩን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከነበረበት ማነቆዎች በማላቀቅ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ባለፉት አስርተ አመታት የገጠር ልማት እስትራተጂ ተነድፎ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቶአል፡፡በዚህም መሰረት በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ አመርቂ ውጤቶች ማስመዝገብ ተችሎል፡፡የአርሶ አደሩን የግብርና ልማት ለማፋጠን ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን በማስፋት ስትራቴጂው አማካይነት ለሁሉም አርሶ አደሮች ለማዳረስ፣ ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና የመስኖ ልማት ለማካሄድ እንደዚሁም ከፍተኛ ዋጋ የሚያስገኙ የግብርና ምርቶች ወደማምረት ለማሸጋገር ስልት ተነድፎ ርብርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም የአነስተኛ አርሶ አደር የመኸር ሰብል ምርት በ2002 ከነበረበት 180 ሚልዮን ኩንታል በ2006 ወደ 270 ሚሊዮን ኩንታል በማደግ የ90 ሚልዮን ኩንታል ጭማሪ ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡የማስፋት ስትራቴጅያችን በተሟላ መንገድ ባለመፈፀሙና ይህንን ለማሳካት የሚያስችለን የሠራዊት ግንባታ ሥራችን በአምስት

ዓመቱ ውስጥ በሙላት ባለመገንባታችን ከመሠረታዊ አማራጭ ዕቅድ ከማሳካት አልፈን የግብርናን ተጨማሪ እሴት (GDP) በእጥፍ በማሳደግ የከፍተኛ የዕድገት አማራጭ ላይ እንደርሳለን ያልነውን ማሳካት አልቻልንም፡፡ በዚህ ደረጃ መፈፀም አሁንም የቤት ሥራችን ይሆናል፡፡

በግብርና ዘርፍ ሌላው ከተቀመጠው ግብ በላይ የላቀ አፈፃፀም የተመዘገበበት የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት ሥራ ነው፡፡በዚህም መሠረት የውሃ፣ የአፈር፣ የስነ-ህይወታዊ ሃብታችንን የሚያጐለብቱ የማህበረሰብ የተፋሰስ ልማቶች በዕቅድ ከተያዘው በላይ ተከናውነዋል፡፡ የተጐዱ አካባቢዎች ከሰውና ከእንሰሳት ንክኪ ነፃ በማድረግ እንዲያገግሙ ተከልለው ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጐላቸዋል፡፡የአፈር መከላትን የሚከላከሉና የውሃ ሥርገትን የሚያጐለብቱ የማህበረሰብ ተፋሰስ የመሠረተ-ልማት ግንባታዎች ከዕቅድ በላይ ተከናውነዋል፡፡የተራቆቱ አካባቢዎችን ዘርፈ ብዙ ጥቅም በሚሰጡ የዛፍ ዝርያዎች በመሸፈን እንዲያገግም የተደረገው የመሬት ስፋት ከዕቅዱ በላይ ከ12 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ደርሷል፡፡ እነዚህ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት ሥራዎችን በመከተል አነስተኛ የአርሶ አደር መስኖዎችን የማስፋፋት ሥራ የተከናወነ ሲሆን ከ2 ሚልዮን ሄክታር በላይ ማልማት ወደሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡

የአርብቶ አደሩን የአኗኗር ዘይቤ ተከትሎ የእንሰሳት ሃብት ልማቱን ይበልጥ ውጤታማና ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር በመከላከል ላይ የተመሠረተ የእንሰሳት ጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ፣ የውሃና ግጦሽ አቅርቦት እንዲሻሻል እና የግብይት ሥርዓቱ እንዲጠናከር ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ሌላው የአርብቶ አደሩን ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተና መስኖን ማዕከል ያደረገ ልማት በስፋት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

### 1.1.3. የፖለቲካዊ ሁኔታ

በአገራችን የዲሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባትና መልካም አስተዳደር በማስፈን የህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሰፊና ውስብስብ ትግል ተከሂደል።በዚህም መሰረት ህዝቡ ለተከታታይ በተካሄዱ ሃገራዊ ምርጫዎች ላይ በነቂስ ወጥቶ መሳተፍ የቻለበት፡በተለያዩ መድረኮች ሀሳቡን/እምነቱን ያለምንም መሸማቀቅ የሚናገርበት፤የምርቱ እንዲሁም የንብረቱ ባለቤት የሆነበት፤የዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቱ የተከበረበት ስርአት መገንባት ተችሎአል፡፡ መልካም አስተዳደርን በማስፈን፣ የህዝብ ተሳትፎን በማረጋገጥ፣ ቀልጣፋና ከሙስና የፀዳ ባህል በመፍጠርና ሙስናን

በቁጥጥር ሥር በማስገባት ለእድገት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ታቅዶ ስተገበር መቆየቱ ያታመናል። ሆኖም ግን በሚጠበቀው ውጤት ልክ ማሳካት ባለመቻሉ በዲሞክራሲ ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደር፣ በኪራይ ሰብሳቢነት፣ በግልጸኝነት፣ በተጠያቂነትና ፈጣንና ፍትሃዊ አገልገሎት ከመስጠት አኳያ ያልተሻገርናቸው በርካታ ተግዳሮቶች ይታያሉ።

ከዚህ በመነሳት በሁለተኛው የዕድገትና ትርንስፎርሜሽን ዕቅድ በዋናነት በአገራችን የተጀመረውን የዲሞክራሲ ሥረዓት ግንባታ ለማስቀጠል፣ የመልካም አስተዳደር ላመስፈን፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ፍታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተማማኝ በሆነ መሠረት ላይ ለማቆምና አገራችንን የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ ትምህርት ቤቶችን ማዕከል የደረገ ፓኬጅን መተግበር አስፈልጓል።

## 1.2. ከሁኔታ ትንተና የተወሰዱ መደምደሚያዎችና ዋና ዋና ጉዳዮች

መንግስት የገጠሩን ህብረተሰብ ትራንስፎርም ለማድረግ የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ እስትራቴጂዎችንና ፓኬጆችን በመቅርጽ ተግባራዊ እየደረገ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሻሻል ላይ ይገኛል። በሰብል ልማት ላይ በተሠረው ሥራ በአገር ደረጃ ራሳችንን ለመቻል በቅተናል። የእንሰሳት ሀብት ልማትም ለረጅም ጊዜ ንቅናቄ ሳይታይበት የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ለውጥ እየታየበት ነው። ከሁሉም በላይ ድግሞ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ያስመዘገብነው ስኬት የገጠሩን ሕዝብ ለላቀ ሥራ ያነሳሳ ነው። የተጀመረው ወጣቱን ማዕከል ያደረገ የገጠር ሥራ ፈጠራ ፕሮግራም መዘርጋቱ ሌላው ተስፋን የጫረ እርምጃ ነው።

ይሁን እንጅ አሁንም ቢሆን አብዛኛው አርሶ አደር ከፍተኛውን የግብርና ምርታማነት ያረጋገጠ አይደለም። በአርሶ አደሩ ዘንድ የቴክኖሎጂ መጠቀም ፍላጎት የሚፈለገው ደረጃ ላይ አልደረሰም። በተለይ ቴክኖሎጂና ግብአቶችን በምክረ ሀሳቡ መሠረት ያለመጠቀም፣ የታካችነት ችግር መኖሩ፣ ከኃላቀር አስተሳሰቦች ያለመላቀቅ ችግሮች ያታያሉ።

የገጠሩን ኅብረተሰብ በማስተማርና በማሰልጠን ኑሮዉን ለመሻሻልና የአኗኗር ዘይቤውን ለመለወጥ እንቅስቃሴዎች እየተደርጉ ቢሆንም የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓታችን ከተለያዩ አገልግሎት አሠጣጥ ሂደት ጋር ባለመቀናጀቱና ትምህርትና

ስልጠና በቀጥታ በምርት ላይ ለተሰማራዉ ለገጠሩ ህብረተሰብ በሚፈለገዉ አግባብ ተደራሽ ባለመደረጉ የሚፈለገውን ያህል ውጤት አልተመዘገበም።

በመሆኑም የገጠሩን ህብረተሰብ ሕይወት ትራንስፎርም ለማድረግ ከመሬት ጥገኝነት ዉጪ ሌሎች አማራጭ የስራ መስኮችን በትምህርትና ስልጠና በመታገዝ መፍጠር አስፈልገል። ስለሆነም የገጠሩን ህብረተሰብ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ትራንስፎርም ለማድረግ ጥራት ያለዉ የትምህርት ስልጠና አቅርቦት ከሌሎች መሰረታዊ የገጠር ልማት ክንውኖች እንዲሁም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶች ጋር በማጣመር ማቅረብ የግድ ይላል፡፡ የገጠሩን ህብረተሰብ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ለመቅረጽ እንዚህን ክንውኖችና አገልግሎቶች በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ትምህርት ቤቶችን ማእከል በማድረግ መስጠት የጎላና ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## 1.3. የፓኬጁ አስፈላጊነት

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች የተለዩ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትኩረት ተሰጥቶት መታቀዱ ይታወቃል፡፡ ይህን ዕቅድ በተጠናከረ መልኩ በመተግበር የገጠሩን ኅብረተሰብ የኑሮ ዘይቤ ትራንስፎርም ለማድረግ ትምህርት ቤቶችን ማዕከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ይህ ፓኬጅ በዋናነት በተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የነበረውን ያልተጠናከር ቅንጅታዊ አሰራር በማስወገድና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማኅበራትና የባለሀብቶችን ተሳተፎ በማሳደግ የመንግሥት ልማታዊ አቅጣጫዎችን በመከተል ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ሀገራዊ እድገት ለማስቀጠል አሰፈላጊነቱ የጎላ ነው፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች የሚገኘውን የተማረ የሰው ኃይልና የተደራጀ ግብዓትን ለሀገር እድገትና ልማት በመጠቀም ጎልማሶች የዕለት ተዕልት ኖሯቸውን ለማሻሻልና ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ተግባሮችን ለመከወን የሚያስችሉ የማንበብ፣ የመፃፍ፣ የማስላት ክህሎቶችንና የተግባር ስልጠናዎችን እንዲያዳብሩ ለማስቻል የፓኬጁ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ስለሆነም ትምህርት ቤቶችን ለውጥ አስተናጋጅ ተቋማት በማድረግ ጎልማሶች ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የተሻሻሉ አሰራሮችን በማስረፅ የገጠሩን ኅብረተሰብ የኑሮ ዘይቤ ትራንሰፎርም

ለማድረግ ፓኬጁ ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ እውቀቶችና ክህሎቶችን በማዳበር የእድሜ ልክ ትምህርትን ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ሴቶችና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ባገነዘበ ሁኔታ በሁሉም ክልሎች በማስፋፋት የተመጣጠነ ዕድገት ለመፍጠር እንዲቻል ይህ ፓኬጁ አስፈልጓል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2.1. የፓኬጁ ዓላማ

### 2.1.1. አጠቃላይ ዓላማ

ትምህርት ቤቶችን ማዕከል ያደረገ ፓኬጅ በመተግበር የገጠሩን ኅብረተሰብ የኑሮ ደረጃና የአኗኗር ዘይቤ በመለወጥ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማፋጠን፡፡

### 2.1.2. ዝርዝር ዓላማ

- ❖ የሥራ ፈጣራን ያማከለ አማራጭ የትምህርትና ስልጠና አቅርቦት በስፋት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፣
- ❖ የዲሞክራሲ ሥርዓትን በመገንባት መልካም አስተዳደር ማረጋገጥ፤
- ❖ ዘመናዊና አዳደስ ቴክኖሎጅዎችን በማስተዋወቅ ምርትና ምራታማነትን ማሳደግ፣
- ❖ በቅድመ መከላከል ላይ ያተኮረ የጤና ትምህርት ከኅብረተሰቡ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ጋር አያይዞ በመስጠት ጤናማ ኅብረተሰብ እንዲኖር ማገዝ፣
- ❖ አዋጪ በሆኑ የገቢ ማስገኛ ተግባሮች ላይ የገጠሩ ኅብረተሰብ እንዲሰማራ በማድረግ የመሬት ላይ ጥገኝነትን መቀነስና የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲኖራቸው ማስቻል፣
- ❖ ዘመናዊና አዳደስ የቤት አሰራሮችንና የአኗኗር ዘዴዎችን በገጠሩ ኅብረተሰበ እንዲተገበሩ ማስቻል፤
- ❖ ት/ቤቶች የኅብረተሰቡ ባህላዊና ስፖርታዊ ክብረ-በዓሎች ማስተናገጃ ማዕከል እንዲሆኑ ማስቻል፣
- ❖ የተፈጥሮ ሀብትን በመንከባከብ የኅብረተሰብን ተጠቃሚነት በማሳደግ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አካባቢን እንዲፈጠር ማስቻል፣

- ሴቶች በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፍ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑና መብቶቻቸውን እንዲያስከብሩ እንድሁም በየደረጃው ውሳኔ ሰጭ ቦታዎች እንዲመጡ ማገዝ፣

## 2.2. ትምህርት ቤቶችን ማእከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን በጎልማሶች ትምህርትና ስልጠና ዋና ዋና የትኩረት መስኮች

### 2.2.1. የንባብና የጽህፈት ክህሎትና የሙያ ስልጠናዎች

- የንባብ፣ የጽህፈትና የስሌት ክህሎት
- የተለያዩ አጫጭር የሙያ ስልጠናዎች
- የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የገበያ አመራረጥና ቁጠባ

### 2.2.2. የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና መልካም አፈስተዳደር

- ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ግዴታዎች ማወቅ
- የኪራይ ሰብሳቢነትን ምንጮች፤ መገለጫዎችና መከላከያዎቹ
- መከባበር፣ መቻቻልና ግጭቶችን በውይይት የመፍታት

### 2.2.3. የጤና አጠባበቅ

- የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ
- የቤተሰብ ጤናና ዘመናዊ አኗኗር
- በሽታን መከላከልና መቆጣጠር

### 2.2.4. እርሻና ተፈጥሮ ሀብት

- የተፈጥሮ ሁበት ልማት
- ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴዎችና የቴክኖሎጅ አጠቃቀም

### 2.2.5. የእንሰሳት እርባታ

- ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ
- የዓሳ እርባታ

### 2.2.6. የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ

- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ
- የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔና መከላከያው
- አማራጭ የኃይል ምንጮችን አጠቃቀም

### 2.2.7. ቱሪዝም፣ ባህልና ቅርስ

- ሪስት መስህቦችን መጠበቅና መንከባከብ
- የኅብረተሰቡን ባህሎች፣ እምነቶች፣ ቱፊቶችና ቅርሶች መጠበቅና መንከባከብ

### 2.2.8. ሥርዓተ ጾታ

- የጾታ እኩልነት
- ሴቶችን ማብቃት፣ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ
- በወጣትነት ወቅት የሚታዩ ችግሮችና መፍትሄወቻቸው

### 2.2.9. ስፖርት፣ ባህላዊ ጫዋታዎችና መዝናኛዎች

- ባህላዊ፣ ስፖርት (የፈረስ ጉግስ፣ ገበጣ፣ የገና ጨዋታ፣ ነጻ ትግል …)
- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ
- የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች
- ድረማ፣ ባህላዊ ጫዋታዎችና ሌሎች ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ ጫዋታዎች
- ልዩ ልዩ ባአላትና ፌስትቫሎች
- ሥነ ጥበብ

### 2.2.10. ማኅበራዊ ደህንነት

- ህገውጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከል
- ማኅበራዊ ችግሮችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል
- የቤተሰብ ደህንነት ጥበቃ

### 2.2.11. ከተማ ልማትና ቤቶች

- ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶች አሰራር
- አካባቢን ማስዋብ

# ክፍል ሶስት

## 3.1. ትምህርት ቤቶችን ማእከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን በጎልማሶች ትምህርትና ስልጠና የትኩረት መስኮች፣ ዝርዝር ይዘቶች፣ የማስፈጸሚያ ሥልቶች፣ ፈጻሚ አካላት፣ የሚፈጸምበት ጊዜና የበጀት ምንጭ

| ተራ ቁጥር | በጎልማሶች ትምህርትና ስልጠና የትኩረት መስኮች | ዝርዝር ይዘቶች | የማስፈጸሚያ ሥልቶች | ፈጻሚ አካላት | የሚፈጸምበት ጊዜ | የበጀት ምንጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የንባብና የጽህፈት ክህሎትና የሙያ ስልጠናዎች | • የንባብ፣ የጽህፈትና የስሌት ክህሎት<br>• የተለያዩ አጫጭር የሙያ ስልጠናዎች<br>• የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የገበያ አመራረጥና ቁጠባ | • የጤና፣ የግብርና ይዘቶችንና የሌሎች የሂይወት ክህሎት ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• ከጤናና ከግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ከመደበኛ መምህርንና ከተቀጣሪ አመቻቾች ጋር አብሮ የመማማሪያ ይዘቶችን በማቀድና በማመቻቸት፣<br>• የመማማሪያ ሰዓቱን በጎልማሶች ፍላጎት በቀን፣ በማታ፣ በርቀት በማመቻቸት መስጠት፣<br>• የንባብ ቤቶችን በማደራጀት የንባብ አገልግሎቶችን መስጠት፣<br>• ምቹ የንባብ አካባቢን (የጤና፣ የግብርናና የሌሎችንም ትምህርታዊ ፖስተሮችንና ማስታወቅያዎችን በመለጠፍ) መፍጠር፣<br>• በአነስተኛ የንግድ አሰራርና በአዋጪ የገበያ አመራረጥ ስልተ ላይ ስልጠና መስጠት፣ | • ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች<br>• የፌደራል ቲ/ሙ/ኤ<br>• ክልል ቲ/ሙ/ኤ<br>• የጥቃቅንና አ/ል/ኢ. | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | • በተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚደራጁበትን፣ የሚቋቋቡበትንና የሚበደሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣<br>• ፕላዝማ፣ ቴሌ ቪዥን፣ ቲፕ ሪኮርደር፣ ሲዲ፣ ራዲዮ ወዘተ መጠቀም፣ | | | |
| 2 | የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና መልካም አፈስተዳደር | • ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ግዴታዎች ማወቅ<br>• የኪራይ ሰብሳቢነትን ምንጮች፣ መገለጫዎችና መከላከያዎቹ<br>• መከባበር፣ መቻቻልና ግጭቶችን በውይይት የመፍታት | • የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• የውይይት፣ የክርክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በማመቻቸት፣<br>• በዘርፉ የተሰማሩ በለሙያዎች በመገበዝ፣<br>• በነዚህ ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረበ<br>• በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥረዓት የዳበረ ልምድ የላቸውን ኅልማሶች በመጋበዝና በማመቻቸት | • ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች<br>• የሲቪክ ማህበራት<br>• ሊጎችና ማህበራት<br>• በየደረጃው የሚገኙ የኮምንኬየሽን ጽ/ቤቶች | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |
| 3 | ጤና አጠባበቅ | • የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ<br>• የቤተሰብ ጤናና ዘመናዊ አኗኗር<br>• በሽታን መከላከልና መቆጣጠር | • የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ፣ የቤተሰብ ጤናና ዘመናዊ አኗኗር እና በሽታን መከላከልና መቆጣጠርን የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ከመደበኛ መምህርንና ከተቀጣሪ አመቻቾች ጋር አብሮ የመማማሪያ ይዘቶችን በማቀድና በማመቻቸት፣<br>• የጤና በለሙያዎችን በመጋበዝና ውይይትን በማመቻቸት<br>• በነዚህ ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረበ | • ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር<br>• ክልል ጤና ቢሮ<br>• ወረዳ ጤናጽ/ቤት<br>• የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች<br>• የሲቪክ ማህበራት<br>• ሊጎችና ማህበራት | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | • ፕላዝማ፣ ቴሌ ቪዥን፣ ቲፕ ሪኮርደር፣ ሲዲ፣ ራዲዮ ወዘተ መጠቀም፣ | | | |
| 4 | እርሻና ተፈጥሮ ሀብት | • የተፈጥሮ ሁብት ልማት<br>• ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴዎችና የቴክኖሎጅ አጠቃቀም | • የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴዎችና የቴክኖሎጅ አጠቃቀም የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• ከእርሻና የተፈጥሮ ልማት ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ከመደበኛ መምህርንና ከተቀጣሪ አመቻቾች ጋር አብሮ የመማማሪያ ይዘቶችን በማዘጋጀት፣ በማቀድና በማመቻቸት፣<br>• የግብርና በለሙያዎችን በመጋበዝና ውይይትን በማመቻቸት<br>• በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረበ<br>• ፕላዝማ፣ ቴሌ ቪዥን፣ ቲፕ ሪኮርደር፣ ሲዲ፣ ራዲዮ ወዘተ መጠቀም፣ | • እርሻና ይተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር<br>• የክልል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ<br>• የወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤት<br>• እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ኤክስቴንሽን ሰራተኞች<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |
| 5 | የእንስሳት እርባታ | • ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ<br>• የዓሳ እርባታ | • ዘመናዊ የእንስሳትና የዓሳ እርባታ የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• ዘመናዊ የእንስሳትና የዓሳ እርባታ ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ከመደበኛ መምህርንና ከተቀጣሪ አመቻቾች ጋር አብሮ የመማማሪያ ይዘቶችን በማዘጋጀት፣ በማቀድና በማመቻቸት፣<br>• የግብርና በለሙያዎችን በመጋበዝና | • የእንሰሳትና አሳ ሃብት ልማት ሚ/ር<br>• ክልል የእንሰሳትና አሳ ሃብት ልማት ቢሮ<br>• የወረዳ የእንሰሳትና አሳ ሃብት ልማት ጽ/ቤት<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ውይይትን በማመቻቸት<br>• ዘመናዊ የእንስሳትና የዓሳ እርባታ ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረብ<br>• ፕላዝማ፣ ቴሌ ቪዥን፣ ቴፕ ሪኮርደር፣ ሲዲ፣ ራዲዮ ወዘተ መጠቀም | • ት/ቤቶች | | |
| 6 | የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ | • የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ<br>• የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔና መከላከያው<br>• አማራጭ የኃይል ምንጮችን አጠቃቀም | • የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔና መከላከያው አማራጭ የኃይል ምንጮችን አጠቃቀም የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ጥበቃ ሰራተኞች፣ ከመደበኛ መምህርንና ከተቀጣሪ አመቻቾች ጋር አብሮ የመማማሪያ ይዘቶችን በማዘጋጀት፣ በማቀድና በማመቻቸት፣<br>• የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ጥበቃ በለሙያዎችን በመጋበዝና ውይይትን በማመቻቸት<br>• የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔና መከላከያው አማራጭ የኃይል ምንጮችን አጠቃቀም ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረብ<br>• ፕላዝማ፣ ቴሌ ቪዥን፣ ቴፕ ሪኮርደር፣ ሲዲ፣ ራዲዮ ወዘተ መጠቀም<br>• የባዮጋዝ አሰራርና አጠቃቀም በተመለከተ የግንዛቤ መድረኮችን በማዘጋጀት | • ደንና የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ሚ/ር<br>• የክልል የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ቢሮ<br>• የወረዳ የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ቢሮ<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |
| 7 | ቱሪዝም፣ በህልና ቅርስ | • የቱሪስት መስህቦችን መጠበቅና | • የቱሪስት መስህቦችን መጠበቅና መንከባከብ የኅብረተሰቡን ባህሎች፣ እምነቶች፣ | • የባህልና ቱሪዝም | ከ2009 - | • መንግስትና |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መንከባከብ<br>• የኅብረተሰቡን ባህሎች፣ እምነቶች፣ ትዉፊቶችና ቅርሶች መጠበቅና መንከባከብ | ትዉፊቶችና ቅርሶች መጠበቅና መንከባከብ የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• የቱሪዝም፣ በህልና ቅርስ ሰራተኞች፣ ከመደበኛ መምህርንና ከተቀጣሪ አመቻቾች ጋር አብሮ የመማማሪያ ይዘቶችን በማዘጋጀት፣ በማቀድና በማመቻቸት፣<br>• ቱሪዝም፣ በህልና ቅርስ በለሙያዎችን በመጋበዝና ውይይትን በማመቻቸት<br>• በአካበቢው የሚገኙ በባህላዊ ትዊፊቶችና ቅርሶች እውቀትና ግንዛቤ ያላቸው ጎልማሶችን ለውይይት በመጋበዝ ማመቻቸት<br>• የባህላዊ ቅርሶችና ትውፊቶችን የሚመለከት ፌስቲቫሎችን ማዘጋጀት<br>• የቱሪስት መስህቦችን መጠበቅና መንከባከብ፣ የኅብረተሰቡን ባህሎች፣ እምነቶች፣ ቱፊቶችና ቅርሶች መጠበቅና መንከባከብ ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረበ<br>• ፕላዝማ፣ ቴሌ ቪዥን፣ ቲፕ ሪከርደር፣ ሲዲ፣ ራዲዮ ወዘተ መጠቀም | ሚ/ር<br>• የክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮ<br>• የወረዳ የባህልና ቱሪዝም<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች | 2017 ዓ.ም | • መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |
| 8 | ሥርዓተ ጾታ | • የጾታ እኩልነት<br>• ሴቶችን ማብቃት፣ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ<br>• በወጣትነት ወቅት የሚታዩ ችግሮችና መፍትሄወቻቸው | • የጾታ እኩልነት፣ ሴቶችን ማብቃት፣ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግን፣ በወጣትነት ወቅት የሚታዩ ችግሮችና መፍትሄወቻቸው የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣ | • የሴቶችና ህጻናት<br>• ጉዳይ ሚ/ር<br>• የክልል ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ<br>• የወረዳ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | • የሴቶችና ህጻነት ሰራተኞች፣ ከሴቶችና ወጣቶቸ ማኅበራት ተወካዮች፣ ከመደበኛ መምህርንና ከተቀጣሪ አመቻቾች ጋር አብሮ የመማማሪያ ይዘቶችን በማዘጋጀት፣ በማቀድና በማመቻቸት፣<br>• ከሴቶችና ወጣቶች ሊግና ማኅበራት ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግንዛቤን ማሳደግ<br>• ከመገናኛ ብዙሀን ጋር በመቀናጅት በአሕዝቦት ሥራ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣<br>• የጾታ እኩልነት፣ ሴቶችን ማብቃት፣ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግን፣ በወጣትነት ወቅት የሚታዩ ችግሮችና መፍትሂወቻቸው በሚመለከቱ ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረበ | • ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች<br>• የሲቪክ ማህበራት<br>• ሊጎችና ማህበራት | | |
| 9 | ስፖርት፣ ባህላዊ ጫዋታዎችና መዝናኛዎች | • ባህላዊ፣ ስፖርት (የፈረስ ጉግስ፣ ገበጣ፣ የገና ጨዋታ፣ ነጻትግል ...)<br>• የአካል ብቃት እንቅስቃሴ<br>• የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች<br>• ድረማ፣ ባህላዊ ጫዋታዎችና ሌሎች ባህላዊና ዘመናዊ የሙዘቃ ጫዋታዎች<br>• ልዩ ልዩ ባአላትና ፌስትቫሎች<br>• ሥነ ጥበብ | • ከስፖርትና ወጣቶች ሚነስቴርና ከስፖርት ፌደሬሽን ጋር አብሮ በማቀድ  ባሃላዊ ስፖርት፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴንና የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች ማመቻቸት፣<br>• ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጋር በመሆን በድራማ፣ በባህላዊ ጫዋታዎች፣ በዘመናዊ ሙዚቃዎችንና በሥነ ጥበበ የሚዝናኑበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣<br>• የሙዚቃ ፌስትቫሎችንና የሥነ ጥበብ ኤግዝቢሽን የሚካሄዱበትን መድረክ ማመቻቸት፣<br>• የውድድር መድረኮችንና ፕሮግራሞችን ማመቻቸት፣<br>• በተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች በመታገዝ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣ | • የወጣቶችና ስፖርት ሚ/ር<br>• የክልል የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት<br>• የወረዳ የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች<br>• የስፖርት ፌደሬሽን | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ማኅበራዊ ደህንነት | • ህገውጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከል<br>• ማኅበራዊ ችግሮችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል<br>• የቤተሰብ ደህንነት ጥበቃ | • ህገውጥ የሰዎች ዝውውርን፣ ማኅበራዊ ችግሮችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የቤተሰብ ደህንነት ጥበቃን የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ጉዳይ ከሚመለከታቸው አካላት (ሠራተኛና መኅበራዊ ጉዳይ፣ ሴቶችና ህጻናት፣ ስፖርትና ውጣቶች፣ የጸጥታ አካላት…) ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማመቻቸት<br>• ህገውጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከል፣ ማኅበራዊ ችግሮችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል፣ የቤተሰብ ደህንነት ጥበቃ በሚመለከቱ ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረብ<br>• የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች መጠቀም | • የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር<br>• የክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ<br>• የወረዳ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |
| 11 | ከተማ ልማትና ቤቶች | • ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶች አሰራር<br>• አካባቢን ማስዋብ | • ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶች አሰራርና አካባቢን ማስዋብ የሚመለከቱ ይዘቶችን ከንባብ፣ ከጽህፈትና ክስሌት ክህሎቶች ጋር አቀናጅቶ የመማማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት መስጠት፣<br>• ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶች አሰራር አካባቢን ማስዋብ ባለያዎችን በመጋበዝ ግንዛበየ ማስጨበጥ<br>• ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶች አሰራር አካባቢን ማስዋብ በሚመለከቱ ይዘቶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለንባቡ አገልግሎት በማቅረብ | • የከተማ ልማትና ቤቶች ሚ/ር<br>• የክልል ከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ<br>• ት/ት ሚኒስቴር<br>• ክልል ት/ቢሮ<br>• ወረዳ ት/ት ጽ/ቤት<br>• ት/ቤቶች | ከ2009 - 2017 ዓ.ም | • መንግስትና<br>• መያዶች<br>• የግል ባለሃብቶች<br>• ህብረተሰቡ |

### 3.2. የውጤት አመላካቾች /የሚጠበቁ ውጤቶች/

ይህንን ፓኬጅ በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ የሚከተሉት ዋና ዋና ውጤቶች ይገኛሉ ተብሎ ይታመናል፡፡እነሱም

- የጎልማሶችን ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢውን አደረጃጀት የፈጠሩ ክልሎች፣ዞኖች፣ወረዳዎች ቀበሌዎች እንዲሁም ትምህርት ቤቶች በቁጥር
- በፓኬጁ ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ የጨበጡ በየደረጃው ያሉ አመራሮች ፈፃሚዎች እንዲሁም ተጠቃሚ ማህበረሰብ ቁጥር ያድጋል
- በፓኬጁ ተጠቃሚ በመሆን ኖሮአቸው የተቀየረ የቀበሌ ነዋሪዎች ቁጥር ይጨምራል
- ለገጠር ትራንስፎርሜሽን የተፈጠሩ ሞዴል የሆኑ ትምህርት ቤቶች በቁጥር
- በተፈጠሩ የገጠር የስራ እድሎች ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶችና ጎልማሶች በቁጥር
- ከማይምነት ነፃ የሆኑ ሴትና ወንድ ጎልማሶች በቁጥር።

# ክፍል አራት

## 4.1. የፓኬጁ ማስተግበሪያ ስልቶች

ት/ቤቶችን ማዕከል የደረገዉ የገጠር ትርንስፎርሜሽን ፓኬጅ የማስተግበሪያ ሥልቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

- ፓኬጁ ከትምህርት፣ ከግብርና ልማት፤ ከጤናና እንዲሁም የሌሎች ልማት መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት የሚተገበር ይሆናል፣
- ቅንጅቱ በአመራር ሰጭነት፣ በሰው ኃይልና በበጀት ምደባ፣ በእቅድ ዝግጅት፣ በትግበራ፣ በክትትልና ድጋፍ ተፈጻሚ ይሆናል፣
- በተደራጀ የልማት ስራዊት አቅም በመንቀሳቀስ ተግባርና ኃላፊነትን መወጣት፣
- ለገጠሩ ትራንስፎርሜሽን የትምህርት አመራሩንና የመምህራንናን ተሳትፎ ማሳደግ፣
- ሞዴል የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማእከል ት/ቤቶችን በመፍጠር ምርጥ ተሞክሮን ቀምሮ ማስፋት፣
- የትምህርት ቤቶችንና የአካባቢውን ማህበረሰብ ትስስር ማጠናከር፣
- በት/ቤቶች መካከል የልምድ ልውውጥ ስርአት መዘርጋት፣
- የህዝብ ክንፍ ማነቆዎችን በመፍታት ለትራንስፎርሜሽኑ ስኬት በጋራ መስራት፣
- ስለ ገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጁ በተለያዩ የንቅናቄ መድረኮች ግንዛቤ በመፍጠር የኅብረተሰቡን ተሳተፎና ባለቤትነት እንዲያድግ ይደረጋል፣
- የትራንስፎርሜሽን ፓኬጁ ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ይውላሉ፤
- በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚዎች የተለያዩ አቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ፣
- ጥራትና ታማኒነት ያለውና ቀልጣፋ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል
- ለትራንስፎርሜሽኑ ፓኬጁ ስኬታማነት ተገቢውን አደረጃጀት ይፈጠራል፣
- ፓኬጁን በመንግስት በጀት ብቻ ለመተግበር ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ በመሆኑ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድረጅቶችን ፣ ሲቭክ ማህበራትን ና የግላ ባለሀብቶችን ያቀፈ ፎረም ማቋቋም፣
- ከቀበሌው ውጭ ያሉ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትቤቶች ኮሌጆችና በአቅራቢያቸው ካሉ ኮሌጆችና የኒቨርስቲዎች ጋር

የሚተባበሩበትና የሚተሳሰሩበት አግባብ በሰፋት ታይቶ የአጋርነት የአፈጻጸም መመሪያ እንዲዘጋጅና የበኩላቸውን ሀገራዊ ሃላፊነትና ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ፡፡

## 4.2. የፓኬጁ ተጠቃሚዎች

ትምህርት ቤቶችን ማዕከል አድረጎ የተዘጋጀውን የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ ተጠቃሚዎች እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆናቸው ሆኖ፡-

- ቀደም ብለው በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያልተሳተፉና ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት የማይችሉ፣
- ማንበብና መጻፍ ችለው በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡ፣ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም በመከታታል ላይ ያሉና ያጠናቀቁ ጎልማሶች፣
- ለችግር ተጋላጭ (Vulnerable) የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የኑሮ ዘይቤያቸው ለመደበኛ ትምህርት መከታተል የማያስችላቸው አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች

## 4.3. ትምህርት ቤቶች ለዚህ ተግባር ለምን ተመረጡ?

ትምህርት ቤቶች አላማቸው ትውልድን በተለያዩ እውቀትና ክህሎት በማነጽ ህብረተሰቡ ኑሮውን በተሻለ ደረጃ እንዲመራ ማስቻል በመሆኑ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማእከል እንዲሆኑ መመረጣቸው ተገቢነት አለው፡፡

ትምህርት ቤቶች የማህበረሰቡ በመሆናቸው በትምህርት ቤቶችና በማህበረሰቡ መካከል ጥብቅ ግንኙነት አለ። ጎልማሶች ስለ ትምህርት ቤቶች ከልጆቻቸው መረጃ ያገኛሉ፣ ይከታተላሉ፣ የልጆቻቸውን ሁኔታ ለመከታተልም ከትምህርት ቤት አመራርና መምህራን ጋር ይመክራሉ፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቶች ማህበረሰቡ በቅርብ የሚከታተላቸው በመሆኑ፣ የትምህርት ባለሙያዎችን በስፋት የያዙ በመሆናቸው ለገጠር ትራንስፎርሜሽን ማእከልነት አመቺ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ትምህርትና ስልጠናውን ማቀድ፣ መምራት፣ ሥርዓተ ትምህርቱን መፈጸም እንዲሁም ሌሎች የመማማሪያ ቁሳቁሶችንም በአግባቡ ማቀናጀት የሚችሉ ባለሙያዎች ስላሏቸው ፓኬጁ ትምህርት ቤቶችን ማእከል አድርጎ ቢተገበር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

ትምህርት ቤቶችን በማዕከልነት ስንጠቀም ለጎልማሶች ትምህርትና ስልጠና የምንጠቀምባቸው የመማማሪያ ቁሳቁሶች/ ቴክኖሎጂዎች/ ለመደበኛው ትምህርት የተጓዳኝ ትምህርትና ስልጠና ግብአት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ትምህርት ቤቶች ማዕከል በመሆናቸው የአካባቢው ማህበረሰብ በመደበኛ ትምህርት ስለሚሰጠው የትምህርት አሰጣጥና ሂደት በቂ ግንዛቤ በመጨበጥ ስለትምህርት ጥራትና ተገቢነት በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያስችለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጎልማሶች ከማህበረሰቡ የመማማር ሂደትና የትምህርት ቁሳቁሶች የህብረተሰቡን ባህል፣ ወግ፣ ታሪክና እሴቶች ጠብቀው ከማስቀጠል ባሻገር ተማሪዎች የትውልድ ቅብብሎሹን ለማስቀጠል ያስችላቸዋል፡፡


እንዲሁም ትምህርት ቤቶች ተደራሽ በመሆናቸው በአካባቢው የሚኖሩ ሴቶችን ተሳትፎ ያሳድጋል፣ ልጆቻቸውንም ወደትምህርት ቤት በመላክና በቅርበት በመከታተልም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

ስለዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በመነሳት ሲታይ ትምህርት ቤቶችን በማዕከልነት መጠቀሙ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ለማፋጠን ዋነኛ መሳሪያ ነው፡፡

### 4.3.1. የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ ለመተግበር በትምህርት ቤቶች የሚኖረው አመራርና አደረጃጀት

ትምህርት ቤቶችን ማእከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ በቅንጅት በመተግበር ሲኬታማ ለመሆን ጠንካራ የሆነ አመራርና አደረጃጀት ያስፈልገዋል።

የቀበሌ ቦርድና ቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊነትና የስራ ድርሻ ከዚህ በፊት በነበረውና ተከልሶ በተዘጋጀው የቦርድና ቴክኒክ ኮሚቴ አሰራር መመሪያ መሰረት የሚቀጥል ሆኖ በትምህርት ቤት ደረጃ የሚኖረው አደረጃጀት የሚለከተለው ይሆናል።




## 4.3.2. በትምህርት ቤቶች የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ ለመተግበር የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነት

ትምህርት ቤቶችን የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ለማድረግ በሚደረገው ሂደት የማህበረሰቡ ተሳትፎ እና ባለቤትነት እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ የባለቤትነት ስሜትና በማእከሉ ቀጣይነት መካከል ጠንካራ ቁርኘት አላቸዉ፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰቡ ይበልጥ በተሳተፈ ቁጥር ይበልጥ ባለቤትነት ይሰማዋል፣ ይህም የፓኬጁን ትግበራ ቀጣይነት በማረጋገጥ ሂደት የሚኖረውን ፋየዳ የጎላ ያደርገዋል፡፡

ያካባቢው ማህበረሰብ የተደራጀ ተሳትፎ ለባለቤትነት መጎልበት ወሳኝ የመሆኑን ያህል የባለቤትነት ስሜት መጎልበት በበኩሉ ለፓኬጁ ቀጣይነት መረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ የማህበረሰብ አባላት ተሳትፎ የሚገለፀዉ በስመ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን በአስተዳደር፣ በአመራርና በእቅድ ዝግጅት እንዲሁም በዉሳኔ ሰጪነት ማህበረሰቡ በንቃት ሲሳተፍ ነዉ፡፡ስለሆነም ትምህርት ቤቶችን ማእከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚቻለው በዋናነት፡-

- ትምህርት ቤቶቹ በማዕከልነታቸው ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ የጎላ ሆኖ ሲገኝ
- አስፈረላጊ ግብአቶችን እንዲሁም አገልግሎቶችን በመጠንና በጥራት አማልተው መገኘት ሲችሉ
- የሚሰጡ አገልግሎቶች የማህበረሰቡን የትምህርትና ሥልጠና ፍላጎቶች የሚያሟሉ መሆን ሲችሉ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ የማህበረሰብ ተሳትፎንና ባለቤትነትን በማጎልበት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ

- የፓኬጁን እቅድና ትግበራ አሳታፊ ማድረግ፣
- ማህበረሰቡ የራሱን ልማት የመቆጣጠር፣ የቅድሚያ ፍላጎቱን ራሱ ለይቶ እንዲወስንና ለችግሮቹ የራሱን መፍትሔዎች እንዲሰጥ ማበረታታት፣
- ማህበረሰቡ ለፓኬጁ ትግበራ የአቅሙን ያህል የቁሳቁስ፣ የገንዘብና የጉልበት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ፣
- ከማህበረሰቡ የተዉጣጡ አባላትን ያቀፈ የማኔጅመንት ኮሚቴ ማቋቋምና ለኮሚቴዉ አባላት በፕሮግራሙ አመራር፣ አስተዳደር፣ እቅድ ዝግጅትና በመሳሰሉት ላይ ስልጠና በመስጠት አቅማቸዉን መገንባትና ለፕሮግራሙ ቀጣይነት የበኩላቸዉን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፣
- የተለያዩ የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በመጠቀም በህብረተሰቡ ዘንድ ተከታታይ ቅስቀሳ ማካሄድ ናቸዉ፡፡

## 4.4. ትምህርት ቤቶችን ማዕከል ያደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ክትትልና ድጋፍ

### 4.4.1. የክትትልና ድጋፍ ዓላማ

- በትምህርት ቤቶች የፓኬጁ ትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ድክመቶችን በመለየት ድጋፍ መስጠት፣
- በክትትልና ድጋፍ የተገኙ አበረታች ውጤቶችንና ጠንካራ ጎኖችን በመለየት እንዲጎለብቱ በማድረግ የልምድ ልውውጥ የሚደረግባቸውን ስልቶች መቀየስ፣
- ፓኬጁ በተጠቃሚ ማኅበረሰብ ኑሮ ላይ ያመጠውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊናፓለቲካዊ ለውጦችን ለመለየትና አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- የተጠናከረ የመረጃ አያያዝና ፍሰት ሥርዓት መኖሩን ለማረጋገጥና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መስጠት፣
- ግልፅነትና የተጠያቂነት ያለው አሰራርን ማስፈን፣
- መልካም ተሞክሮዎችን በሰፋት ማዳረስ።

### 4.4.2. የክትትልና ድጋፍ አግባብ

በየደረጃው ያለው የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ቦረድና የቴክኒክ ኮሚቴ የፕሮግራሙን አፈጻጸም በየጊዜው እየተገናኙ ይገመግማሉ፣ አቅጣጫም ያስቀምጣሉ እንዲሁም የቦርድ አባል መስሪያ ቤቶች በየደረጀው የየሴክተራቸውን እቅድ አፈጻጸም በሚገመግሙበት ወቅት የጎልማሶች ትምህርትን እንደ አንድ ተግባር በመቁጠር አፈጻጸሙን ይገመግማሉ በተጨማሪም በየደረጃው የሴክተራቸውን እቅድ በመስክ በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ሲያደረጉ አብረው የጎልማሶች ትምህርትንም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፣ ግብረመልስም ይሰጣሉ። የማናጅሜት ኮሜቴ አባላት በየጊዜው በመገኘት በፓኬጁ አፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ ያድጋሉ ፣ ግብረመልስም ይሰጣሉ። የአፈጻጸሙን ሪፖርት ለቀበሌው ትምህርትና ስለጠና ቦርድ ያቀርባሉ፡፡ የቀበሌው ትምህርት ስልጠና ቦርድ የፓኬጁን አፈጻጸም በየጊዜው ክትትል በማድረግ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

## 4.5. የግንኙነት መረብ መዘርጋትና አጋርነትን ማጠናከር

የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በቅንጅት ለመምራት የሰው ኃይልን ጨምሮ ሀብትን በጋራ በመጠቀም፣ በማቀድና ክንውኖችንም በመከታተልና በመገምገም ፓኬጁን ውጤታማ ለማድረግ፣ ቦርዱና ቴክኒክ ኮሚቴው ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ ተቋማት ጋር ያለውን የትብብር ደረጃ ማሳደግና በዘርፉ ከተሰማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የልማት አጋሮች ጋር ያለውን የግንኙነት መረብ ማጠናከር ያስፈልጋል። በመሆኑም፣

- በጎልማሶች መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ዘርፍ የተሠማሩ መንግስታዊና መንግሥታዊ ያለሆኑ ድርጅቶችንና ኤጀንሲዎችን እንዲሁም ወደፊት በዘርፉ ለመሰማራት አቅሙና ፍላጎቱ ያላቸውን መለየትና በየደረጃው የአጋሮች የጋራ መድረክ/ፎረምን ማጠናከር፣
- በጎልማሶች ትምህርት የተለያዩ ተግባራትን በተመለከተ ማን ምን ሊያከናውን እንደሚችል ለመወሰን የምክክር አውደጥናቶችን ማካሄድ፣
- በጎልማሶች ትምህርት የሚከናወኑ ተግባራትን ድርሻን ለመውሰድ፣ በጋራ ለማከናወንና በአሠራር ቅደም ተከተል ዝግጅት የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀትና የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም፣

- አሁን ያለውን የግንኙነት መረብ በመጠቀም በየጊዜው ሀሳቦችንና ተሞክሮዎችን ለመጋራት በጋራ ለማቀድና አሠራሮችን ለመፈተሽ የሚያስችል ቋሚና ዘላቂ የውይይት ፎረም ማቋቋም።

የገጠሩን ማህበረሰብ ትራንስፎርም ለማድረግ በየደረጃው የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን እንዲሁም መላውን የገጠር ማህበረሰብ ማነቃነቅ ፡ አቀናጅቶ ማንቀሳቀስና መምራት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪ በፓኬጁ የተካተቱት ጉዳዮች በርካታ በመሆናቸውና የጎ/መ/ያልሆነ የትምህርት ዘርፍ ዘላቂ የህይወት ዘመን ትምህርትነ ስልጠናን የሚያቅፍ ስለሆነይህም አሁን በየደረጃው ባለው መዋቅር ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ጉዳይ ባለመሆኑ ይህንን ታላቅ ሃላፊነት ሊሸከም የሚችል እና በጥናትና ምርምር ላይ ተመርኩዞ ልማትና ትራንስፎርሜሽንን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ሀራዊ ግቦችን ለመተግበር የሚያስችል ራሱን አዲስ የቻለ መዋቅት መዘርጋት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**ተቀፅላ**

**ት/ቤቶችን ማእከል ባደረገ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ፓኬጅ ዝግጅት ላይ ተሳታፊ አካላት**

| ተ.ቁ | የተወከሉ መስሪያ ቤቶች | የተሳታፊ ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1. | ትምህርት ሚኒስቴር | 8 | |
| 2. | ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | 2 | |
| 3. | እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር | 1 | |
| 4. | እንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር | 1 | |
| 5. | ደንና አካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር | 1 | |
| 6. | ሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር | 1 | |
| 7. | የሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴር | 1 | |
| 8. | ንግድ ሚኒስቴር | 1 | |
| 9. | የከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር | 1 | |
| 10. | የፌደራል ቴ/ሙ.ያ/ትም/ት ስልጠና ኤጀንሲ | 1 | |
| 11. | አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ | 1 | |
| 12. | ደ/ብ/ብ/ህ ክልል ትምህርት ቢሮ | 1 | |
| 13. | ኢሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ | 1 | |
| 14. | ትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ | 1 | |
| 15. | ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ | 1 | |
| 16. | ዲቪቪ ኢንተርናሽናል | 1 | |
| 17. | ጀኔቫ ግሎባል | 1 | |
| አጠቃላይ ድምር | | 25 | |